

# በቶሮንቶ፤ ካናዳ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተሰጠ መግለጫ

የሀገራቸው ዳር ድንበር መደፈርና የሕዝባቸው ስቃይ የቀረቀራቸው በቶሮንቶ፤ ካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ግንቦት 18 ቀን 2008 ዓ/ም ባደረጉት ስብሰባ በወያኔ ድብቅ ሴራ በምዕራብ ኢትዮጵያ ከጎንደር እስከ ጋምቤላ ድረስ የሚገኘው ለም መሬት ለሱዳን በመሰጠቱ የሱዳን ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ሕዝባችንን እያሰሩና እያንገላቱ ንብረቱን እያወደሙና እያፈናቀሉት በመሆኑ የተሰማቸውን የቁጣ ስሜት የገለጹ ሲሆን አባቶቻችንና አያቶቻችን በደማቸውና ባጥንታቸው አስከብረው ያቆዩልን አገር ወያኔ ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ሕዝቧን ለማዋረድ ሲል የሚያደርገውን ተከታታይ ጥፋት ተቀምጠን የማንመለከትና ከሕዝባችን ጎን በመቆም የአገራችንን ሉዓላዊነት የምናስከብር መሆኑን በአንድ ቃል ተናግረዋል።

ከ1600 ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ያለውና እንደየአካባቢው ከ30 ኪሎሜትር በላይ ወደ ውስጥ ዘልቆ የሚገባውን ለም ክፍል አስረክቦ ምንም ነገር እንዳልተፈጠረና "ተቃዋሚዎች የሚያስወሩት የሀሰት ዜና ነው" በማለት ይህን ግዙፍ ጥፋት ከሕዝብ ለመደበቅ ቢሞክርም ሀቁ እየወጣና እየታየ በመሆኑ መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያንቀሳቅስ የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት አማራጭ የሌለው አጣዳፊ ተግባር በመሆኑ በሌሎች አገሮችና አካባቢ ካሉት ኢትዮጵያውያን ጋር መረጃ ለመለዋወጥና ትግሉን ከዳር እስከዳር ለማንቀሳቀስ እንዲቻል አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩን እንዲከታተልና የጋራ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ቤቱ በአንድ ድምጽ ተስማምቷል።

ወያኔ መቼም ቢሆን ለኢትዮጵያ አንድነትና ዳር ድንበር መከበር ቆሞ የማያውቅ በመሆኑ ይህንን አገር አጥፊ ቡድንን ማስወገድና በምትኩ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የሆነ የሕዝብ መንግሥት መመስረት ብቻ ቋሚ መፍትሔ መሆኑን አበክሮ ገልጿል።

ይህ የሚቋቋመው ኮሚቴም ለአንድ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ሥራ ሳይሆን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በማሰባሰብና በአንድነት አንቀሳቅሶ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስጠበቅና ከሕዝብዋ ጎን ቆሞ የሚጠበቅበትን የዜግነት ድርሻ እንዲወጣ የሚያመቻች መሆኑም ታውቋል።

በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በወያኔ የውስጥ ስምምነት ለሱዳን መሰጠቱን በማውገዝና በመቃወም ትግሉን በአገር አቀፍ ደረጃ አስተባብሮ የሚጠበቅብንን የዜግነት ድርሻ ሁሉ ለመወጣት በአንድነት የተነሳን መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ትግል ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኖራለች!

በቶሮንቶ የምንገኝ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን